# እንደ ሸሚዝ የሚቀያየር የፖለቲካ እምነትና አቋም

## ክፍል አንድ

በሸዋይልማ ኪዳኔ (ጀርመን)

*“... ጠቅላይ ሚኒስቴር መለሰ ዜናዊ ሰላማዊ ሰው እንጂ የሚነቀፉ ሰው ሊሆኑ አይገባም። ... ጠ/ሚ/ሩ የኢትዮጵያም ሆነ የፓርቲያችን ጠላት አይደሉም።...“*

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ
መስከረም 16 ቀን ፍራንክፈርት ከተማ ላይ
በተካሄደ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ካደርጉት ንግግር

በቅርቡ በአሜሪካ ሜሪላንድ ክ/ሀገር ሮክቪል ከተማ በአስራ አምስት የኢትዮጵያ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የተቋቋመው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲጠይቀዉና ሲጠብቀው የነበረውን ጥያቄ የመለሰና የተቃዋሚ ድርጅቶችን ትግል የሚያጠናክርና አንድ እርምጃ ወደፊት ሊያስኬድ የሚችል ጅምር በመሆኑ ሕዝቡ ለህብረቱ ያለዉን ድጋፍና አድናቆት በአገኘው አጋጣሚ እየገለጸ ነው። በእርግጥ ይህ ህበረት ለኢትዮጵያ የተቃዋሚ ድርጅቶች የመጀመሪያው ህብረት ባይሆንም ከዚህ በፊት ከነበሩት የተቃዋሚዎች ህብረት የሚለየው ነገር ቢኖር በራሳቸው በተቃዋሚዎቹ ደርጅቶች አነሳሽነት ለሁለት ዓመት ዝግጅት ተደርጎበት በከፍተኛ ጥንቃቄ የተካሄደ በመሆኑና ከሁሉም በላይ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በተናጥል የሚያደርጉት ትግል የትም ሊያደርሳቸው እንደማይችል የተገነዘቡ መሆናቸዉን ያረጋገጠ በመሆኑ ከፍተኛ ተስፋ በህብረቱ ላይ እንድንጥልበት አድርጓል። እኔን በግሌ በኩል የተቃዋሚዎች ህብረት መቋቋምን ያህል የሚያስጨንቀኝ ነገር ቢኖር የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችን ማንነትና የአቋም ጽናታቸውን ማወቅን ጭምር ነው። አንድ የተቃዋሚ ድርጅት መሪ ወይንም ታዋቂ ፖለቲከኛ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግር ከፍ አድርጎ በመስበኩና ወያኔን በመቃወሙ ብቻ ጆሮአችንንና ልባችንን ከፍተን የምነሰጠው ከሆነና ለቆመለት የፖለቲካ ዓላማ ምን ያህል የአቋም ጽናት እንዳለው ሳንፈትሽና ሳናጤን የምንደግፈው ከሆነ ባልጠበቅነው ቀንና ሰአት በሚያሳየን የፖለቲካ አቋምና የእምነት ለውጥ የምናተርፈው ነገር ቢኖር መገረም፣ ማዘንና መቆጨት ብቻ መሆኑን የምናውቀው ጉዳይ ይመስለኛል። እንዲያው የሩቁን ትተን የቅርቡን ብናነሳ እንኳን የአፋር አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር (አርዱፍ) የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና በአውሮፓ የአርዱፍ ተጠሪ የነበሩት አቶ ሞሀሞዳ አህመድ ጋስ ድርጅቱን ከድተው በድብቅ ወደ አዲስ አበባ መመለሳቸውን ድርጅቱ በኦክቶበር 21 ቀን 2002 ዓ.ም ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫው ለሕዝብ አሳውቋል። አቶ ሞሀሞዳ ጋስ በጠንካራ ፀረ ወያኔ አቋማቸውና በአንደበተ ዕርቱነታቸው በኢትዮጵያዊያን ዘንድ ከፍተኛ ዝናና አድናቆት አትርፈው እንዳልነበር ባልተጠበቅ ቀን ድርጅታቸውን ከድተው የኢትዮጵያን የግዛት ሉአላዊነትና አንድነት ካስደፈር በተለይም በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምነውን የአፋር ሕዝብ የዜግነትና ሰብአዊ መብት በማስደፈር፣ ኢትዮጵያዊያን አፋሮችን ያለፍላጎታቸው በሸዕቢያ አገዛዝ ሥር እንዲተዳደሩ ካደረገና ከሸዕቢያ ጋር በመተባበር የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር ታጋዮችን ከወጋና ካስወጋ አምባገነን የወያኔ መንግስት ጋር ያብራሉ ብሎ የጠበቀ አልነበረም።

አንድ ፖለቲከኛ የአባላቱንና የደጋፊዎቹን ከዚያም አልፎ የፖለቲካ ተቃዋሚዎቹን ከበሬታና አድናቆት ማግኘት የሚችለው ለፖለቲካ እምነቱ በቆራጥነት ያለማወላወል ሲታገል እንደሆነ መናገሩ መድገም ካልሆነብኝ በስተቀር አዲስ ነገር እንዳልሆነ በሚገባ እገነዘባለሁ። ፖለቲካም ተለዋዋጭ ክስተት እንደመሆኑ የፖለቲካ እምነትም ሊለውጥ እንድሚችልም ጠንቅቆ ይገባኛል። በተቃዋሚው የፖለቲካ ጎራ ውስጥ በሚገባ ያላወቅናቸው ብዙ አቶ ሞሀሞዳ ጋስ ሊኖሩ እንደሚችሉ ጥርጥር የለኝም። በመሆኑም የሕዝቡ የመጀመሪያው ተግባር መሆን የሚገባው የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችን ማንነትና ለቆሙለት ዓላማ ያላቸውን ጽናት ከመረመርንና ከፈተሽን በኋላ ወይ መደገፍ አላያም ማግለል መልመዱን በተለይም የአቋም ጽናት የሌላቸውን በግልጽ የማግለሉን ባህል መጀመር ይኖርብናል። የፖለቲካ እምነታቸውንና አቋማቸውን ከትናንት ዛሬ፤ ከዛሬ ነገ ለመቀየር የማይቸግራቸው ምን እንደሚፈልጉ ለማወቅ እስኪያቅተን ድረስ ግራ የሚያጋቡ ፖለቲከኞች በተቃዋሚው ጎራ የመኖራቸውን ያህል ለቆሙለት ፖለቲካ ጊዚያቸውን፣ ገንዝባቸውን፣ እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን በሙሉ አሳልፈው የሰጡና ፖለቲካን እንደ ሁለትኛ ትዳራቸው አድርገው አጥብቀው የያዙና የኢትዮጵያን ሕዝብ መከራና ስቃይ አገር ውስጥ ከሕዝቡ ጋር አብረው ወይም ደግሞ ከአገር ውጭ በርቀት የሕዝቡን ኑሮ በልቦናቸው የሚኖሩ ልባችንን ስጥተን አይናችንን ጨፍነን ልንከተላቸው የምንችል የተቃዋሚ ፖለቲከኞችም አሉን።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ግን የፖለቲካ እምነታቸውን እንደፈለጉ ለመቀየር የማይቸግራቸው፣ አቋማቸውን በሌላው ላይ ለመጫን የማይፈሩ፣ የፖለቲካ ድርጅትን ዝቅ አድርጎ እንደ ግልንብረትነት ለማየት የሚፈልጉ

ፖለቲከኞችን የሚመለከት ነው። እንደነዚህ ዓይነቱ ፖለቲከኞች ፖለቲካን ቲያትር ያስመስሉታል። ጥያቄው ፖለቲከኞቻችንን ምን ያህል እናውቃችዋለን? የሚል ነው። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ይህን ጥያቄ ለመመልስ አንድን ፖለቲክኛ በምሳሌነት እንዲያቀርብ ይገደዳል። አስገራሚ የሆነ የአቋም መለዋውጥ ከሚታይባቸው "በተቃዋሚ የፖለቲካ ጎራ" ውስጥ ከሚገኙ ፖለቲከኞች ውስጥ ከመድኅን ፓርቲ አንጃ በመፍጠር የተገለሉት ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በአሁኑ ሰዓት በዋነኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ጥቃቅን የሆነ ስህተት ተፈጥሮ አንባብዬን እንዳላሳስተው በመፍራትና ተናጋሪውንም በቀጥታ መጥቀሱን የመረጥኩ በመሆኑ አንዳንድ ጥቅሶችን እንዳሉ በእንግሊዘኛው ማስቀመጡን መርጫለው። እንደዚሁም የቀን አቆጣጠርን በተመለከተ አንዳንድ ቦታ ላይ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በሌላ ቦታ ደግሞ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የምጠቀም መሆኑን አንባቢው ከወዲሁ እንዲረዳልኝ እጠይቃለሁ። መቼስ ሰው ሆኖ የማይሳሳት የለምና ከስህተቴ ለመማርና ለማወቅ ዝግጁ መሆኔን እየገለጽኩ ጥቃቅን ስህተት ከሆነ አንባብዬ ስህተቴን እያረመ እንዲያነበው እያሳሰብኩ በሌላ በኩልም የለም ሙሉ በሙሉ መልስ ያስፈልገዋል ብሎ የሚያምንም አንባቢ ካለ ደግሞ እኔንም አንባቢውንም ለማረም የራሱን ጽሑፍ ያቀርባል ብዬ አምናለሁ። ፖለቲካ አንዳንድ ጊዜ ከቦክስ ስፖርት ጋር በጣም ስለሚመሳሰል ማጥቃት፣ መከላከል፤ መልሶ ማጥቃት አንዱ ገጽታው መሆኑም ይገባኛል።

## ደርግ

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ የደርግ ስርአትን ከድተው አሜሪካን ጥገኝነት ሲጠይቁ ያ ሰው በላ ስርአት የ12 ዓመት ዕድሜ የነበረው ሲሆን ኮ/ሉ ከዘጠኝ ዓመት አገልግሎት በኋላ ነበር የተለዩት። ኮ/ል ጎሹ በደርግ ሥራአት ውስጥ ካገለገሉ እጅግ በጣም ጥቂት ከሆኑና በጣት ከሚቆጠሩ ስመ ጥር ተወዳጅና የተከበሩ ፖለቲከኞች ውስጥ አንዱ የነበሩ ሲሆን ደርግን ከድተው በዚያው በሄዱበት አሜሪካ ሲቀሩ የኢትያጵያ ሕዝብ ፦

*"የጥንቸሏ መሞት የአጋዘኑ መድከም ሲያንገበግብሽ፣*
*ይኸውና ዛሬ ጎሹም ጠፋልሽ። "*

ብሎ የተገጠመላቸው እውቅ ኢትያጵያዊ ናቸው።

ኮ/ል ጎሹ አገር ወዳድ ከሆኑ ኢትያጵያዊያኖች ጋር በመሆን መድኅንን መስርተው ድርጅቱን በሊቀመንበርነት በመሩበት ወቅት ለአንዳንድ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች በሚጽፏቸው ደብዳቤዎች ላይ የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) ሊቀመንበር ከሚለው በተጨማሪ በኩራት (ተገቢም ነው) የቀድሞው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር የሚለውን የሹመት መጠሪያ አብሮ በመጻፍ በኩራት ሲጠቀሙበት በሌላ በኩል ደግሞ ይህን የማዕረግ ስም እንዲያገኙ ያደረገውን የደርግ ወታደራዊ መንግስት እንዳይሸጥ እንዳይለውጥ እያደርጉ ሲያጣጥሉትና ሲተቹት ለሚሰማ ሰው በዚያ መንግስት ውስጥ አንድ ቀን እንኳን ያገለገሉ አይመስሉም። የደርግን ሥርዓት ሲተቹ፦

*" ... በ1966 ዓ.ም የዘውድ አገዛዝ ሲወድቅ የተደራጁ የሕዝብ ፓርቲዎች ስላልነበሩ ሥልጣን በደርግ አምባገነኖች ተነጥቆ ለ17 ዓመታት ሕዝቡ ወደር ለማይገኝለት ጭቆናና እልቂት ተዳርጎ ቆየ።...*

*ቃለ ምልልስ ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ ጋር*
*ሩሕ 1985 ዓ.ም*

በቀድሞ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓት ወስጥ ያገለገሉ ኢትዮጵያዊያኖች የቀድሞ አምባሳደሮችና ጠቅላይ ሚኒስተር ማዕረጋቸውን በኩራት ሲጠቀሙበት ብቻ ሳይሆን የሥርዓቱን ድክመት በመተቸት ጠንካራ ጎኑንም በመከላከል ሥርዓቱን በማገልገላቸውና በተጨማሪም ለአገራቸው ባበረከቱት አስተዋጽኦ ዛሬም ድረስ ይኮራሉ። በእውነቱ ትክክልም ይሁን ወይም የተሳሳተ ፖለቲከኞች ለእምነታቸው ሲኖሩ የወዳጆቻቸውንም ሆነ የተቀናቃኞቻቸውንም አድናቆትና ከበሬታ ያገኛሉ። እኔ እንደ አንድ ተራ ዜጋ ኮ/ል ጎሹ ያገለገሉት የደርግ ሥርዓት በኢትያጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሰውን ጥፋት ወደ ጎን ትተን ምን መልካም ተግባር ሠርቷል ብለህ ታምናል ተብዬ ብጠየቅ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻንና የኢትያጵያን የብሔረሰቦች ኢንስትቲዩት ማቋቋሙ መልካም ተግባራት ናቸው ብዬ በግሌ አምናለሁ። በእርግጥ ኮ/ል ጎሹ ወልዴም ቢሆኑ ለርዕሰ ብሔሩ ለኮ/ል መንግስቱ ኃይለማርያም በጻፉት የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ ውስጥ፦

*"... ባለፉት 12 መራራ የትግል ዓመታት አብዮታችን ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፏል፤ በሠፊው ሕዝብ መሥዋዕትነት አስከፊው የፊውዳል ሥርዕት ተገርስሶ ወድቆ መሬት የብዝበዛ መሣሪያ መሆኑ ቀርቷል፤ ሕዝቡ በሁሉም ደርጃ እንዲንቀሳቀስ ተደርጓል፤ አብዮቱ ከፀረ አብዮተኞች ቅልበሳ ድኗል። ..."*

በማለት ለአብዮቱ የነበራቸውን አድናቆትና ሥርዓቱን በማገልገላቸው የሚኮሩ መሆኑን አይሸሽጉም። ኮ/ል ጎሹ በዚህ የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ ላይ እኔን በግሌ እጅግ በጣም የሚገርመኝና አልገባ እያለ የሚያስቸግርኝ ቃል ቢኖር ኮ/ል ደርግን በሕዝብና በሠራዊቱ የተመረጠ መንግስት ዓይነት አድርገው ሲገልጹ የሚከተለውን ይሉናል።

*"… እንዳንድ በአመራር አካባቢ ያሉትና ግብረአብሮቻቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሎ ያስገኘውን አብዮት እንደግል ንብረታቸው በመቁጠር በአብዮቱ ስም ሲነግዱና ሲንደላቀቁ ይታያሉ። <u>በስልጣን ቁንጮ ላይ ያስቀመጣቸው ሠፊው ሕዝብና ጀግናው መለዮ ለባሽ መሆኑን ዘንግተው</u> ሕዝቡን መናቅና ማንኳሰስ፣ ቆራጥነቱንና ታጋሽነቱን መፈታተን፣ ብልህነቱንና ታሪክ ሰሪነቱን መካድ አይነትኛ ተግባራቸው አድርገውታል።*

ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ የተወሰደ

ሰረዙ የእኔ ነው። እንግዲህ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቦታ እየመረጡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የደርግ ሥርዓትን ስለሚተቹ ወይም ስለሚደግፉ በደርግ ሥርዓት ላይ ያላቸውን ቁርጥ ያለ አቋም ማወቅ ያስቸግራል።

አንዳንድ ጊዜ ትልልቅ ሰዎች ፈጽሞ ይቅር ሊባል የማይችል ትልቅ ስህተት ይፈጽማሉ። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ለሥራ ወጥተው በዚያው በሄዱበት አሜሪካን ከቀሩ በኋላ የሥራ መልቀቂያና የስንብት ደብዳቤ ለኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም ከጻፉ በኃላና በተለይም ደርግ ሊወድቅ መንገዳገድ ሲጀምር በድፍረት በአደባባይ ላይ በኃይለኛ ቃላት ሥርዓቱን ሲተቹ የሰማ ሰው መልሰው ከኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም ጋር ይነጋገራሉ ብሎ እንኳን በእውኑ በህልሙም አያሰበውም። እኔ በግሌ የስማሁትን ለመቀበል በጣም የቸገረኝ ቢሆንም በኮ/ል ጎሹ በራሳቸው የተነገረ በመሆኑ ጆሮዬን ከማመን ውጭ ሌላ አማራጭ የለኝም። ኮ/ል ጎሹ እኤአ ኦክቶበር 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተካሄደው የመድኅን ስድስተኛው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ስለትጥቅ ትግል ምን ያህል እንደደከሙ ለተሰብሳቢው በጉባዔ ፊት ሲናገሩ፦

*"… የትጥቅ ትግላችንን ለማጠናከር ከእኔ የበለጠ የደከመ የለም። ከፍተኛ ጥረት አድርጌአለሁ። መንግስቱ ኃ/ማርያም ሠራዊታችንን በገንዘብ እንዲረዳ ጠይቄው ላስብበት ብሎ ጊዜ እንድሰጠው ጠየቀኝ፣ እንደሚረዳኝ እሺ ብሎኝ በመካከላችን የነበረው ችግር ጠሩን እኔ ካልመራሁት ስላለኝ መስማማት አልቻልንም። …"*

ብለው ነበር። እኔ በግሌ የኮ/ል ጥረት ባለመሳካቱ እንዴት እንደተደስትኩ ለመግለጽ ይቸግረኛል። ኮ/ል ጎሹ የጉባዔው ተሳታፊና ይህን ንግግር የሰሙ የመድኅን አባላት ምን ያህል እንደታዝቧቸው ይህን ጽሑፍ ሲያነቡ እንደሚገለጽላቸው ጥርጥር የለኝም።

## <u>አብሮ የመስራት ችግር</u>

አንዳንድ የድርጅት መሪዎች በመካከላቸው ያለውን አለመግባባት ከፍተኛ ግምት ስለሚሰጡት ወደ ጥላቻ አድጎ የአገርን ጉዳይ አስቀድሞ በሚያግባቡ ጉዳዮች ላይ ተስማምቶ የመስራቱ የፖለቲካ ጥበብ በንድፈ ሃስብ ደርጃ ይቀራል። በፖለቲካ ዓለም  ውስጥ በአንድ አገር ውስጥ ያለውን ሁኔታ ለመቀየር ይቻል ዘንድ፣ ሁኔታዎችን ለማመቻቸተን የሕዝብን ድጋፍ ለማግኘት ከሌሎች  ድርጅቶች ጋር በመተባበር ካልሆነ በስተቀር በግል የትም መድረስ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የሚፈለገው ግብ ላይ እስኪ ደረስ ድረስ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ያለውን የአመለካከትና በመሪ ግለሰቦች መካከል ያለውን አለመግባባት ወደ ጎን በማድረግ በሚያግባቡ ነጥቦች ላይ ተስማምቶ አብሮ እጅና ጓንት ሆኖ በመስራት ህብረት ፈጥሮ መንግስት መቀየርና የሕዝብ ድጋፍ ያለው መንግስት ሥልጣን ላይ ማስቀምጥ እንደሚቻል ማንበብ ብቻ ሳይሆን ማየት እንደሚቻል እሩቅ ሳንሄድ ጥሩዋ ጎረቤታችን የሆነችው ኬኒያ ውስጥ የዳንኤል አርፕሞይ መንግስት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተግባር አሳይተውናል።

ኮ/ል ጎሹ ከሀገር ከወጡ በኋላ የተቃዋሚውን የፖለቲካ መድረክ የተቀላቀሉት ድርጅት ወክለው ሳይሆን በግል የኢዴሐቅ (COEDF) አባል በመሆን ነው። ኮ/ል ጎሹ ላይ አብሮ የመስራት ችግር ብግልጽ ይታይባችዋል። ኮ/ል ክኢዴሐቅ መሪዎች ጋር በጊዜው ያደርጉ የነበሩትን የቃላት ልውውጥ የሰማ ወይም ያየ ወደፊትም ቢሆን አብረው ሊሰሩ እንደማይችሉና አብረው የስሩበትንም አጭር ጊዜ አብረው ሰርተው ነበርን? ብሎ ራሱን እየደጋገም እንዲጠይቅ አድርጓል። ኮ/ል ጎሹ ኢዴሐቅን ሲተቹ፦

*"… COEDF is for the EPRP and MEISON what the EPRDF is for the TPLF — a cover to advance their political agenda, and, I had no wish to engage in a conspiracy of deception of the Ethiopian people …"*

*Col. Goshu Wolde*
Ethiopian Review, Nov. 1992

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከሐምሌ 19 ቀን እስከ ሐምሌ 23 ቀን 1995 በአሜሪካ ሜሪላንድ ክ/ሀገር ሮክቪል ከተማ የተካሄደውን የፖለቲካ ድርጅቶች ጉባዔ ገና ሳይጀመር የማጥላላት ዘመቻ የከፈቱበት ያለ ምክንያት አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ መድኅን የጉባዔው ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን የጉባዔው አዘጋጅ ኮሚቴ ከነበሩት ስምንት ድርጅቶች ውስጥ አንዱ በመሆኑና በኮሚቴው ውስጥ በድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባል በሆኑት በሻለቃ አሰፋ መሸሻ በኩል ተወክሎ ለጉባዔው መሳካት ደፋ ቀና በማላት ለጉባዔው መሳካት ከፍተኛ ጥረት እንዳደረግ ኮ/ሉ በሚገባ ያውቃሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ፕ/ር ስዩም ገላዬ የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) ሊቀመንበር የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የፋይናንስ ጉዳይ ሃላፊና የህብረቱ የሥ/አ/ኮሚቴ አባል መሆናቸው በጣም ያበሽቃቸዋል። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ደግሞ ከመድኅን

የተገነጠለው አንጃ መሪ በመሆን ራሳቸውን ሹመው የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን ማንም የሚያውቀው ጉዳይ ነው።

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከመድኅን ብቻ ሳይሆን ከተቃዋሚው የፖለቲካ ድርጅቶች መድረክ ላይ መገለሉ ከፈጠረባቸው ብሽቀትና ንዴት በመነሳት ቃላት መምረጥ እስኪያቅታቸው ድረስ የዋሽንግተኑን ኮንፈረንስ በማጥላላት ኢ.ሕአፓ የጠራው ጉባዔ ይመስል ሕዝቡ በጉጉት የጠብቀውን ጉባዔ ሲያጥላሉ:-

*"... በህብረት ሽፋን ኢ.ሕአፓን ወደ አምባገነናዊ ሥልጣን የሚያወጣ ድብቅ ሴራ ከሆነ መድኅን በጥብቅ ይታገለዋል። አምባገነናዊ የወያኔ ኢ.ህአዴግ ስርዓት ተወግዶ በምትኩ ትኩስ ዕብሪትኛ አምባገነናዊ የሆነ ድርጅት፣ አገርና ሕዝብ የሚጎዳ ሕዝባችንን እንደገና ለደም መፋሰስና መተላለቂያ ሜዳ የሚዳርግ ድርጅት ስልጣን ላይ እንዲቀመጥ አንፈልግም ... "*

ከኢ.ትዮጵያዊነት ሬዲዮ ጣቢያ ጋዜጠኛ ጋር ካደረጉት ቃለ ምልልስ
እኤአ አውጉስት 10 ቀን 2003 ዓ.ም

በማለት ኢ.ሕአፓ ስልጣን ከሚይዝ ወያኔ በስልጣን ላይ ቢቆይ ይሻላል ብለው ይነግሩናል። ኮንፈረንሱን ኢ.ሕአፓ ያዘጋጀውና የኢ.ሕአፓን ፍላጎት ለማሳካት ብቻ የተዘጋጀ አድርጎ ማቅረቡ በተዘዋዋሪ ሌሎችን በጉባዔው ላይ የተሳተፉትን 14 ድርጅቶች በሙሉ በኢ.ሕአፓ የሚታዘዙና የራሳቸው ህልውና የሌላቸው በሚመስል መልኩ ኮንፈረንሱን የሚያጥላሉበትን ቃለ ምልልስ የሰማ ሁሉ፣ እኚህ ሰው ምን ነካቸው እስከ ማለት ደርሷል። የግሉም ፕሬስ የኮ/ሉን የጥላቻ ዘመቻ በተመለከተ ሲዘግብ:-

*"... የሁሉም ፓርቲዎች ኮንፈረንስ ምናልባትም ከዚህ ቀደም ከተካሄዱት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ህብረትና ቅንጅት በተለየ ብዙዎቹን ተቃዋሚዎች ወደ መተማመን ሊያቀርባቸው ይችላል ሲሉ አንዳንድ ወገኖች እየገለጹ ባሉበት ሁኔታ ከመድኅን በአንጃነት የውጣውና የእነ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ነው እየተባለ የሚጠራው ሌላው መድኅን ያልተጠራበት በመሆኑ ስብሰባውን የሚያጨናግፍ ዘመቻም በነርሱ በኩል እየተካሄደ ስለመሆኑ .... "*

ዘፕሬስ ሐምሌ 9 ቀን 19995 ዓ.ም

በሌላ በኩል ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በዚሁ በኢ.ትዮጵያዊነት ድምፅ ሬዲዮ ቃለ ምልልሳቸው ላይ መድኅን (አንጃው መድኅን) ከተጋበዘ ጥሪውን በደስታ የሚያስተናግድና በጉባዔው ላይ እንደሚገኝና በሌሎችም የኢ.ትዮጵያ ሕዝብ ጉዳዮች ላይ ውይይት በሚደረግባቸው ማንኛውም መድረኮች ላይ እንደሚገኝ ማሳወቅ እወዳለሁ በማለት ኮንፈረንሱን የሚያጥላሉት እንዲሳተፉ ባለመደረጉና በተጨማሪም መድኅን በሊቀመንበሩ በፕ/ሮ ስዩም ገላዬ ተወክሎ በጉባዔው ላይ በመገኘቱ የፈጠረባቸው ንዴትና ብሽቀት ቃለ ምልልሳቸውን እርስ በርሱ የሚጋጩ ቃላቶች የበዙበት እንዲሆን አድርጎታል። ኮንፈረንሱም የመድህንን አንጃ በምን ዓይነት ሎጂክ ሊያስተናግድ እንደሚችል ፈጽሞ አይገባኝም። ጉባዔው በመድረክ ላይ የሚሰራ የፖለቲካ ቲያትር (Political Satire) ቢሆን ኖሮ ባልከፋ ነበር።

## ከሊቀመንበርነት ወደ ፕሬዝዳንትነት

የኢ.ትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) የፓርቲው ፕሮግራም በጥር ወር 1984 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በመጋቢት ወር 1984 ዓ.ም ፓርቲው ተቋቋመ። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በየቃለምልልሱ ሆን ብለው እንድሚሉት የፓርቲው የመጀመሪያ ፕሬዝዳንት ሳይሆን ሊቀመንበር በመሆን ፓርቲውን ለአራት ዓመታት መርተዋል። ኮ/ል ጎሹ ራሳቸውን የአንጃው ፕሬዝዳንት አድርገው በመሾማቸው ስለመድኅን ሲያወሩ ሆን ብለው አድማጭን ለማሳሳትና በድጋሚ በፓርቲው ውስጥ የተመረጡ አስመስሎ ለማቅረብ በኢ.ትዮጵያዊነት ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ ቃለምልልሳቸው ላይ <u>የመድኅን ፕሬዝዳንት</u> ሆኜ ባገለገልኩበት ጊዜ ብለው ይናገራሉ። የለም አድማጭን ለማሳሳት አይደለም ተዘንግቶ ነው ከተባለም ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ የሚከተለውን ለመጥቀስ እወዳለሁ።

*" ... በተጨማሪ የኢ.ትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ የዋሽንግተን ዲሲ የፖስታ ሳጥን ቁጥር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዚህ በታች የሚከተለው የፖስታ ሳጥን በተጨማሪ መከፈቱን በአክብሮት አሳስባለሁ።*

MEDHIN
P.O.Box 13875
Silver Spring, MD 20911-3865
USA

ጎሹ ወልዴ
ሊቀመንበር
ታህሣሥ 12 ቀን 1986 ዓ.ም

ሌላው አንባቢ እንዲያውቀው የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር የኢ.ትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) መሠረታዊ ሰነድ ሁለት (መተዳደሪያ ደንብ) ወስጥ ፕሬዝዳንት የሚል ቃል ፈጽሞ የሌለ መሆኑን ነው። የፓርቲው ፕሮግራም መሠረታዊ ሰነድ አንድ በመባል የታወቃል። የመድኅን ፓርቲ ሊቀመንበር

በጠቅላላ ጉባዔው የተመረጡ ከፍተኛ የአመራር ኃላፊ ሲሆኑ በሴክሬታሪያቱ አማካኝነት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ በማለት የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ክፍል አራት አንቀጽ 16 የሊቀመንበሩን ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር ይገልጻል። የአንጃው ፕሬዝዳንት ኮ/ል ጎሹ ወልዴን የኢትዮጵያ የግሉ ፕሬስ ውጤቶች እሳቸው እንደሚፈልጉት የመድኅን ፕሬዝዳንት እያሉ ሳይሆን የመድኅን የአንጃው መሪ፣ አንዳንዶቹም አንጃ የሚለውን ቃል በውስጠ ታዋቂነት ለመጠቀም እንዲረዳቸው ሆን ብለው የጎሹ ወልዴ እያሉ መጠቀማቸው በራሱ የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቡድን እውቅና ሊሰጠው የፈለገ የሌለ መሆኑን በግልጽ ያሳያል። እስኪ የግሉ ፕሬስ ስለ "ፕሬዝዳንቱ" ሲያትት የሚጠቀምበትን አባባል አብረን እንመልከት።

> *"... ከመድኅን በአንጃነት የወጣውና የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ነው እየተባለ የሚጠራው መድኅን ..."*
>
> ዘፕሬስ ሐምሌ 9 ቀን 1995 ዓ.ም
>
> *"... የመድኅን አንጃ በመሆን የተገነጠሉት ግለሰቦች ..."*
>
> ዘፕሬስ ሐምሌ 19 ቀን 1995 ዓ.ም
>
> *"... የኮ/ል ጎሹ ወልዴ መድኅን ..."*
>
> ሳተናው ሐምሌ 21 ቀን 1995 ዓ.ም
>
> *"... የ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ መድኅን ..."*
>
> ከማትሚኖ ነሐሴ 2 ቀን 1995 ዓ.ም

አንጃው እ.ኤ.አ በአፕሪል 19 ቀን 2003 ዓ.ም ታሪካዊ ጉባዔ እያለ እራሱን የሚያታልልበትን ጉባዔ ባካሄደ ማግስት ባወጣው መግለጫ ላይ መተዳደሪያ ደንቡ ላይ ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ የሚያስችል ለውጥ አደርኩ ብሎ ሲነግረን የአንጃውን መሪ ግን የትኛውን አንቀጽ መሠረት በማድረግ ፕሬዝዳንት ብሎ እንደሾማቸው ሊነግረን አልፈለገም። መግለጫው ሲያትት፡-

> *"... the conference amend the armed struggle clause (Art. 9.4) of the party. ... Goshu Wolde was elected president of Medhin. ..."*
>
> April 21, 2003

ከዚያ በኋላማ ምን ያልተባልነው ነገር አለ። ፕሬዝደንቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የአዲስ ዓመት በዓል እንኳን አደረሳችሁ መግለጫ ሰጡ ተብሎ የአስር ደቂቃ ንግግር በኢንተርኔት ሬዲዮ አደርጉ።

## <u>ድርጅት እንደ ግል ንብረት</u>

የመድኅን ፓርቲ በተመሠረተ በዓመቱ በ1985 ዓ.ም የፓርቲው ሊቀመንበር ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ለኢትዮጵያ ሕዝብና በተለይም ለመለዮ ለባሾች ጥሪ ብለው በካሴት አሳትመው ሲበትኑ ዜናው ለኢትዮጵያ ህዝብና መለዮ ለባሾች ብቻ ሳይሆን ለፓርቲውም ጭምር አዲስ ዜና ነበር። የክተት ጥሪው ከመድኅን ፓርቲ ሳይሆን ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ ብቻ የተላለፈ መሆኑን ካሴቱን በመረጃነት ማቅረብ ይቻላል። በክተት ጥሪ ውስጥ አንድም ቦታ ላይ የመድኅን ስም አይጠራም። ኮ/ል ጎሹ የክተት ጥሪውን (የትጥቅ ትግሉን) የፓርቲው የስ/አ/ኮሚቴ እንዲያፀድቅላቸው ጠይቀውና አፀድቀው በሁለተኛ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ ተሻሽሎ በሰኔ 25 ቀን 1986 ዓ.ም በወጣው ሁለተኛ መሠረታዊ ሠነድ የትጥቅ ትግሉ በክፍል ሶስት አንቀጽ 9.4 እንዲካተት በማድረግ መድኅን የእሳቸው የግል ፍላጎት የነበረው የጦርነት አዋጅ ተጭኖበት ወደ አዲስ የትግል ምዕራፍ ውስጥ እንዲገባና የትጥቅ ትግል ስልትን እንዲከተል ተደረገ። ስለዚህም የትጥቅ ትግሉ (የክተት ጥሪ) በኮ/ል ጎሹ በመድኅን ላይ የተጫነ የግል እምነት እንጂ የፓርቲው አመራር አባላት እንዲሁም የፓርቲው ተራ አባላትና ደጋፊዎች ተወያይተውበትና ደግፈውት የተወሰነ ያለመሆኑን ኮ/ል ጎሹ እያወቁ ዛሬ ከፓርቲው ስለተሰናበቱ ብቻ ምንም ዓይነት መሠረት የሌለው ምክንያት እየደረደሩ ሊያስተባብሉ ሲሞክሩና የፓርቲውን አመራር በጦረኝነት በየአደባባዩ ሲከሱ ሳዳመጠ በጣም ይገርመኛል።

ሌላው ሳልጠቅስ ማለፍ የማልፈልገው ጉዳይ ቢኖር በወቅቱ ክርክርና ጥያቄ ያስነሳው ጉዳይ ቢኖር የኮ/ል ጎሹ የክተት ጥሪ የተላለፈበ ጊዜ ነበር። በወቅቱ የኢትዮጵያ ችግር አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል ብለው የሚያምኑ በርካታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መድኅንን ጨምሮ በፓሪሱ ኮንፈረንስ ተስማምተው አዲስ አበባ ውስጥ የሰላምና የእርቅ ጉባዔ ለማካሄድ ወስነው አንድ አስተባባሪ ኮሚቴ ያቋቋሙበት ጊዜ ነበር። የፓሪሱ ህብረት ዋናው አስተባባሪ ኮሚቴ በአዲስ አበባ ውስጥ ቅርንጫፍ ኮሚቴ አቋቁሞ የኮሚቴው ተወካይ እንዲሆኑ ዛሬ በወያኔ እስር ቤት እየተሰቃዩ የሚገኙትን የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ የሆኑትን ፊታውራሪ መኮንን ዶሪን መምረጡ አይዘነጋም። ጉባዔውን ከጠሩት ውስጥ መድኅንም የአስተባባሪው ኮሚቴ አባል የነበረ ሲሆን የእርቅ ጥሪውን ለኢሕአዴግ ካስተላለፈ በኋላ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ የኢትዮጵያ ህዝብ በኢሕአዴግ ላይ እንዲነሳና እንዲዘምት ጠየቁ። ይህ የኮ/ል ጎሹ የጦርነት አዋጅ መድኅን የአስተባባሪው ኮሚቴ አባል ቢሆንም የህብረቱ አስተባባሪ ኮሚቴ የክተት ጥሪውን እንደማይደግፍ ለማስገንዘብ በመገደዱ በመድህን ላይ መግለጫ

እንዲሰጥበት አስገድዶት ነበር። በወቅቱ መድኀን በአንድ በኩል የሰላም ጥሪ በሌላ በኩል ደግሞ የጦርነት አዋጅ በማሰማቱ የፓርቲው የፖለቲካ አካሄድ ብዙዎቹን ኢትዮጵያውያኖችና የህብረቱን አባል ድርጅቶች ሳይቀር አስገርሞ ነበር። በአጭሩ የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ተግባር ፓርቲውን እጅግ በጣም የጐዳና በአንዳንድ መንግስታት ዘንድ አንድ ሰሞን በአሸባሪነት እስከመታየት አድርሶት እንደነበረ የጀርመን መድኀን ቅርንጫፍ አባላት ጠንቅቀው የሚያውቁት ጉዳይ ነው።

ዛሬ ደግሞ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከዘጠኝ ዓመት በኋላ በካሴት ሳይሆን አንድ ገጽ ከግማሽ በሆነውና በራሳቸው የእጅ ጽሑፍ የተጻፈ " የሰላም አዋጅ" አዘጋጅተው በጥቅምት 9 ቀን 1995 ዓ.ም በፓርቲው ስድስተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ይዘው በመቅረብ "አዋጁን" ጉባዔው እንዲያጸድቅላቸው ጠየቁ። "የአዋጁ" ርዕስ "የኢትዮጵያ መድኀን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባዔ ስድስተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ይላል"። በገጽ ሁለት ላይ ውሳኔውን በተመለከተ በተራ ቁጥር አንድ ላይ የሚከተለው ይነበባል፦

1. በመድኀን መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9.4 ላይ የሰፌው ተሻሽሎ፣ ከእንግዲህ ወዲህ መድኀን አምባገነኑን የወያኔ/ኢሕአዴግ አመራርና ሥርዓት፣ በፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፣ ድርጅታዊና በመሳሰሉት ሰላማዊ መንገዶች እንዲታገል፣

ይልና በመቀጠል ተራ ቁጥር ሁለትን አስነብቦን በመጨረሻ የጠቅላላው ጉባዔው ስድስተኛ መደበኛ ስብሰባ ወስኗል ይላል።

ኮ/ል ጎሹ የዘነጉት ጉዳይ ቢኖር የዛሬው መድኀን በፖለቲካ የበሰለ፣ ውስጠ ዲሞክራሲያዊ አሰራር ያለውና ለግለሰቦች ሳይሆን ለብዙሃን እምነት የሚገዛ አመራር ያለው መሆኑን ሲሆን የሚገርመው ደግሞ የአመራሩ አካል አባል ሆነው ይህንን ግምት ውስጥ ማስገባት አለመቻላቸው ነው። ጉባዔው በኮ/ሉ "የአዋጅ" ረቂቅ ላይ ተወያይቶ ያሳለፈውን ዉሳኔ አባላትና ደጋፊዎች በሰፌው ተወያይተውበትና ጥናት ተካሂዶበት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሚጠራ ጉባዔ ላይ እንዲወሰንበት ስምምነት ላይ ተደርሶ ይህንን ዉሳኔ መሠረት በማድረግ ጉባዔው አምስት አባላት ያሉበት አንድ ኮሚቴ ሲያቋቁም ኮ/ል ጎሹ እንደ የጦርነት አዋጁ ለምን ያለማወላወል ተቀባይነት አላገኘም በሚል አኮረፉ። ከጥቅምት 9 ቀን 1995 ዓ.ም (October 19.2002) ጠቅላላ ጉባዔ በኋላ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከጥቂት ግብረአብሮቻቸው ጋር በመሆን ከፓርቲው ደንብና ሥርዓት ውጭ በመንቀሳቀሳቸው የፓርቲው አመራር ኮ/ል ጎሹንና ግብረአብሮቻቸው የሆኑትን ዶ/ር ሞገስ ገ/ማርያምና አቶ ቸሩ ተፈራን ከድርጅቱ ያባረረ መሆኑን በየካቲት 19 ቀን 1995 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳወቀ። መግለጫውም በመድኀን ሬዲዮ ተላለፈ። የግሉ ፕሬስ ዉጤቶችም ዜናውን ለሕዝቡ ዓይንና ጆሮ አደረሱ።

> *"እነ ጎሹ ወልዴ ተባረሩ"*
>
> *" … የድርጅቱን ህልውና ተፈታትነዋል ያላቸውን ኮ/ል ጎሹ ወልዴንና ግብረአበሮች ናቸው ያላቸውን ማሰናበቱን ፓርቲው በመግለጫው አሳወቀ። … "*

ዘፕሬስ የካቲት 26 ቀን 1995

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ጥቂት በጣት የሚቆጠሩ ሁኔታው በቅጡ ያልገባቸው አባላትንና አንዳንድ በተፈጥሮአቸው ግለሰብ አምላኪነት የሚያጠቃቸውን ግለሰቦች ሰብስበው እ.ኤ.አ በአፕሪል 19 ቀ 2003 ዓ.ም ራሳቸውን የአንጃው ቡድን ፕሬዝዳንት አድርገው ሾሙ። ኮ/ል ጎሹ ራሳቸውን ሊቀመንበር ብለው እንዳይሾሙ የኢትዮጵያ መድኀን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኀን) ሊቀመንበር ክቡር ፕ/ር ስዩም ገላዬ መሆናቸውን ሳር ቅጠሉ ሳይቀር ጠንቅቆ የሚያውቀው ጉዳይ በመሆኑ በቃል ደረጃ የሚያስደስትና ለሹመት ቀረቤታ ያለው ፕሬዝዳንት የሚል የሹመት ቃል ለራሳቸው በመስጠት የቡድኑ መሪ መሆናቸውን አሳወቁ። በኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሚመራው ቡድን የኮ/ሉ የግል ፍላጎት የሚንጸባረቅበት፣ በቅጡ ያልተደራጀና ውይይት እንግዳ የሆነበት ስብስብ መሆኑን ለማሳየት አንድ ምሳሌ ልጥቀስ። "የጎሹ ወልዴ መድኀንና ኢዴአፓ ለውህደት ተስማሙ" የሚለውን ዜና ያንጃው ቡድን አባላት ከአቶ ቸሩ ተረፈና፣ ዶ/ር ሞገስ ገ/ማርያምና ሶስትና አራት ከሚሆኑ የአንጃው አባላት በስተቀር የተቀሩት በሙሉ እንደ እኔው ያነበቡት ከኢንተርኔት ላይ ነው። የአንጃው የኢንተርኔት ሬዲዮ እንኳን ሰንብቶ ነው እንደ አዲስ ዜና ይዞ ለቡድኑ አባላት ጆሮ ያደረሰው።

… ይቀጥላል